[**Employers**: This is a sample employee notice employers can use to inform their employees about earned sick and safe time as required under Minnesota Statutes § 181.9447, subdivision 9. Instructions for completing this notice are in brackets. Delete all instructions before providing this to the employee.]

# ሰራተኞች የህመምና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚያስረዳ ማስታወሻ

የሚኖሶታ ሰራተኞች ደሞዝ እየተከፈላቸው የህመምና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ የማግኘት መብት አላቸው። በዓመት ውስጥ ቢያንስ እስከ 48 ሰዓታት የሚደርስ፣ ለእያንዳንዱ የሰሩበት 30 ሰዓታት፣ ደሞዝ የሚከፈልበት ቢያንስ የአንድ ሰዓት የህመምና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ ማጠራቀም ይችላሉ፡፡ [If you are using a more generous accrual system or a front-loading system, edit the previous sentence and insert the applicable system for the employee who will receive this notice.] አሰሪው፣ በዓመት ውስጥ ሰራተኛው ምን ያህል የህመምና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ እንዳጠራቀመ የሚያውቅበት መንገድ፡ [Note here how you define the accrual or benefit year for the employee. Examples include the calendar year, year by work anniversary or another 12-month period.]

ሰራተኛው፣ ምን ያህል የህመምና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ እንዳጠራቀመና ከዚህም ውስጥ በቅርቡ ምን ያህሉን እንደተጠቀመበት የሚያስረዳ ጽሁፍ ከክፍያው ጋር ተያይዞ መሰጠት አለበት። ልክ የሰራበት ሰዓታት ክፍያ በክፍያ ወረቀቱ ላይ እንደሚገለጸው ሁሉ ይሄው ሰራተኛው ያጠራቀመው የህመምና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ ክፍያም በወረቀት መገለጽ አለበት። ሰራተኛው የሰራው ስራ በሰዓት እንደሚታሰብለት ለዚህ ለህመምና ለደህንነት ጥበቃ ፈቃድ የሚከፈለው ክፍያም በሰዓት መታሰብ አለበት። ሰራተኞች ያጠራቀሙትን ፈቃድ ለመጠቀም ከስራ ሲቀሩ እነሱን ተክቶ የሚሰራ ሰው የማግኘት ሃላፊነት የላቸውም። ያጠራቀሙትን የእረፍት ሰዓታት ከፈለጉ ሁሉንም፣ ካልፈለጉ ደግሞ ምን ያህል እረፍት እንደሚያስፈልጋቸው ራሳቸው ገምግመው ቆጥበው ወይም ቀንሰው የመውሰድ መብት አላቸው።

የተጠራቀመ የህመም ወይም የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ ለሚከተሉት ጉዳዮች መጠቀም ይቻላል፡

- ሰራተኛው የአንጎል ወይም የአካል ህመም ሲያጋጥመውና ለመታከም ወይም ይህንን ለማስወገድ እንክብካቤ ለማድረግ
- የሰራተኛው የቤተሰብ አባል የአንጎል ወይም የአካል ህመም ሲያጋጥመውና ለመታከም ወይም ይህንን ለማስወገድ እንክብካቤ ለማድረግ
- በሰራተኛው ወይም በቤተሰቡ አባል ላይ የቤተዘመድ ጥቃት (domestic abuse)፣ ወሲባዊ ጥቃት (sexual assault) ወይም በቀጣይነት የመከታተል ጥቃት (stalking) ሲደርስ
- ሰራተኛው የሚሰራበት ቦታ፣ ወይም የሰራተኛው የቤተሰብ አባል ትምህርት ቤት ወይም መዋእለ ህጻናት በመጥፎ የአየር ብከላ ወይም በመላው ህዝብ ላይ በደረሰ ድንገተኛ አደጋ ምክንያት ሲዘጋና
- አንድ ሰራተኛ ወደ ስራው ቦታ ቢገባ በያዘው ተላላፊ ህመም ምክንያት ሌሎችን ሊበክል ይችላል ብሎ የህክምና ባለሞያ ውሳኔ ሲሰጥ

## አሰሪን ስለማሳወቅ፣ የጽሁፍ ማረጋገጫ ስለማምጣት (documentation)

አንድ ሰራተኛ ያጠራቀመውን የህመመና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ ለመጠቀም ሲፈልግ በተቻለ መጠን የሰባት ቀናት ማስጠንቀቅያ/ማስታወሻ እንዲሰጠው አሰሪው መጠየቅ ይችላል (ለምሳሌ ቀደም ሲል ቀጠሮ የተያዘበት የሃኪም ቀጠሮ ሲኖረው)። ሰራተኛው፣ ካጠራቀመው የህመመና የደህንነት ጥ ፈቃድ ከሶስት ቀናት በላይ በተከታታይ መውሰድ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ አሰሪው ይህንን ከስራ የመቅረቱን ምክንያት በዝርዝር የሚያሳይ ወረቀት ከሚመለከተው እንዲያመጣ ሰራተኛውን ሊጠይቅ ይችላል።

[The following is an example of an employer policy for employees to provide notice before using earned sick and safe time. Edit the following text to match your company’s policy.] አንድ ሰራተኛ፤ ቀጠሮ ካለው፤ የበሽታ መከላከያ እንክብካቤ ካስፈለገው ወይም ከሚፈቀዱት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ካጋጠመውና መቼ ከሰራ መቅረት እንደሚጀምር ቀኑን የሚያውቀው ከሆነ፤ በተቻለ መጠን አስቀድሞ፤ ቢያንስ ከ [number between one and seven] በፊት ለ[name or position] በ [phone, email or other communication] ማሳወቅ አለበት።

## የበቀል እርምጃ ስለመውሰድ፣ ቅሬታ የማቅረብ መብት

አንድ አሰሪ፤ ሰራተኛው የህመም ፈቃድ ወይም የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ በመጠየቁ ወይም ይህንን መብቱ የሆነውን የፈቃድ ግዜውን በመጠቀሙ በሰራተኛው ላይ የሆነ ዓይነት የበቀል እርምጃ ወይም ማንኛውም ዓይነት አሉታዊ እርምጃ ቢወስድ በህግ ያስጠይቀዋል። አንድ ሰራተኛ ይህንን ፈቃድ በመውሰዴ ወይም በመጠየቄ ፈቃዱን እንዳላገኝ ተከልክያለሁ ወይም የበቀል እርምጃ ተወስዶብኛል የሚል እምነት ካለው አቤቱታውን ወይም ቅሬታውን ወደ ሚኖሶታ የስራና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር (Minnesota Department of Labor and Industry) ማቅረብ ይችላል። በተጨማሪም የዚህ የህመምና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ የማግኘቴ መብት ጠጥሷል የሚል ከሆነ ፍርድ ቤትም ክስ ሊያቀርብ ይችላል።

## ለተጨማሪ መረጃ

በስልክ ቁጥር 651-284-5075 በመደወል ወይም ወደ ሚኖሶታ ስራና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በ esst.dli@state.mn.us ኢሜል በመጻፍ ወይም የሚኒስቴሩን ዌብፔጅ በ dli.mn.gov/sick-leave በመግባት መገናኘት ይችላሉ።

ይህ የሚከተለው ዶኩመንት አቀጣጠሮን በሚመለከት አስፈላጊ መረጃ የያዘ ነው። ስለዚህ ይህንን መረጃ በምን ቋንቋ ማግኘት እንደሚፈልጉ ለማሳየት በግራ በኩል ባለው ባዶ ቦታ (ሳጥን) ምልክት ያድርጉ።

| | | |
|---|---|---|
| | Spanish/Español | Este documento contiene información importante sobre su empleo. Marque la casilla a la izquierda para recibir esta información en este idioma. |
| | Hmong/Hmoob | Daim ntawv no muaj cov xov tseem ceeb hais txog thaum koj ua hauj lwm. Khij lub npauv ntawm sab laug yog koj xav tau cov xov tseem ceeb no txhais ua lus Hmoob. |
| | Vietnamese/Việt ngữ | Tài liệu này chứa thông tin quan trọng về việc làm của quý vị. Đánh dấu vào ô bên trái để nhận thông tin này bằng Việt ngữ. |
| | Simp. Chinese/简体中文 | 本文件包含与您的雇用相关的重要信息。勾选左边的方框将接收以这种语言提供的信息。 |
| | Russian/русский | Данный документ содержит важную информацию о вашем трудоустройстве. Отметьте галочкой квадрат слева для получения этой информации на данном языке. |
| | Somali/Soomaali | Dukumentigan waxaa ku qoran macluumaad muhiim ah oo ku saabsan shaqadaada. Calaamadi sanduuqan haddii aad rabto inaad macluumaadkan ku hesho luqaddan. |
| | Laotian/ພາສາລາວ | ເອກະສານນີ້ມີຂໍ້ມູນທີ່ສຳຄັນກ່ຽວກັບການຈ້າງງານຂອງທ່ານ. ກວດເບິ່ງກ່ອງທີ່ຢູ່ເບື້ອງຊ້າຍເພື່ອຮັບຂໍ້ມູນນີ້ໃນພາສານີ້. |
| | Korean/한국어 | 이 문서에는 귀하의 고용 형태에 관련된 중요한 정보가 담겨있습니다. 이 언어로 이 정보를 받기를 원하시면 왼쪽 상자에 체크하여 주세요. |
| | Tagalog/Tagalog | Ang dokumentong ito ay nagtataglay ng mahalagang impormasyon tungkol sa iyong pagtatrabaho. Lagyan ng tsek ang kahon sa kaliwa upang matanggap ang impormasyong ito sa wikang ito. |
| | Oromo/Oromoo | Waraqaan kun waayee hojii keetii odeeffannoo barbaachisoo ta’an qabatee jira. Saaxinnii karaa bitaatti argamu kana irratti mallattoo godhi yoo afaan Kanaan barreeffama argachuu barbaadde. |
| | Amharic/አማርኛ | ይህ ዶኩመንት አቀጣጠሮን በሚመለከት አስፈላጊ መረጃ የያዘ ነው። ይህንን ዶኩመንት በስተግራ በኩል ባለው ቋንቋ ተተርጉሞ እንዲሰጦት ከፈለጉ በዛው በስተግራ በኩል ባለው ሳጥን ውስጥ ምልክት ያድርጉ። |
| | Karen / ကညီကျိာ် | လံာ်တီလံာ်မီတခါအံၤပာ်ဃုာ်တၢ်ဂ့ၢ်တၢ်ကျိၤအကါဒိၣ်လၢအဘၣ်ဃးဒီးနတၢ်ဖံးတၢ်မၤန့ၣ်လီၤ. တီၤနီၣ်တၢ်ဒၢလၢအစုၣ်စ့ကပၤလၢတၢ်ကဒိးန့ၢ်တၢ်ဂ့ၢ်တၢ်ကျိၤလၢကျိာ်တခါအံၤအဂီၢ်တက့ၢ်. |
| | Arabic/ العربية | يحتوي هذا المستند على معلومات مهمة حول عملك. ضع علامة في المربع على اليمين للحصول على هذه المعلومات في هذه اللغة. |